#DEFYHATENOW

# በይነ-መረብ ላይ የሚፈፀም ስርዓተ ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት



# በይነ-መረብ ላይ የሚፈፀም ስርዓተ ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት

- የሳይበር-ጥቃት (cyber-bullying) እና ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት ምንድነው?
- ወሲባዊ ትንኮሳ ሴቶችን እንዴት በይነ-መረብ ላይ ተፅዕኖ ሊያደርስባቸው ይችላል?
- የሲቪል ማህበረሰብ ድርጊት እና ትምህርት ጠቃሚ የሚሆነው ለምንድነው?

ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት ዓለም ዓቀፍ የጤና እና የሰብዓዊ መብቶች ጉዳይ ሲሆን ዓለም ዓቀፋዊ የሰብዓዊ መብቶችን ህግጋት እና የፆታ እኩልነትን የሚጥስ ነው።

ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት በይነ-መረብ ላይ ብዙ ቅርፆችን የሚይዝ ሲሆን መጥለፍን (hacking)፣ ቁጥጥር ማድረግን፣ ተጠቂዎችን አደገኛ ወደሆኑ ሁኔታዎች ማስቀጠር እና በተንኮል ግላዊ የሆኑ ፎቶዎችን እና መልዕክቶችን ማሰራጨትን ያካትታል።

## በይነ-መረብ ላይ የሚደረግ ማንቋሸሽ ከዲጂታል ዓለም ራስን ማግለልን እና ግለ-ሳንሱርን (self-censorship) ያባብሳል።

ኮልዌ ማጃማ የተሰኘ የአፍሪካ ሚዲያ እና የበይነ-መረብ እና የተግባቦት ከፍተኛ ባለሙያ እንዲህ ይላል፡ በሴቶች ላይ የሚፈፀሙ ቴክኖሎጂ-ነክ የሆኑ ጥቃቶች በፍጥነት እያደጉ መሆናቸው እና እንደ ተራ ጉዳይ እየተቆጠሩ መምጣታቸው በይነ-መረብ መጠቀምን የስርዓተ-ፆታ ጉዳይ እንዲሆን አድርጎታል፡

**"የሳይበር-ደህንነት ክርክሮችን እንደ ሃገር ዓቀፍ እና የክልል የአመራር ፎረሞች ሁሉ ለመንግስት እና ለፋይናንስ/ቢዝነስ ተቋማቱ ከመተው ይልቅ ሴቶችም ግንባር ቀደም ተሳታፊ መሆን እንደሚገባቸው አስፈላጊ መሆኑ ግልፅ እየሆነ መጥቷል።"**

## በይነ-መረብ ላይ የሚደርስ ስርዓተ-ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃትን የሚመለከቱ የህግ ምልከታዎች

ኢትዮጵያ በይነ-መረብ ላይ ስርዓተ ፆታን መሰረት አድርጎ የሚፈፀም ጥቃትን የሚመለከት ህግ የላትም።

## የጳጉሜን ንቅናቄ (አክቲቪዝም) ቅስቀሳ

የተሰኘ ጾታን መሰረት ያደረገ ጥቃትን እና ሌሎች እኩልነት የታጣባቸው ጉዳዮችን ግንዛቤ በሚመለከት በየሎ ሙቭመንት የተዘጋጀ።

**facebook.com/TheYellowMovementAau**

## የሴቶች አመራር እና በይነ-መረብ ላይ የሚደረግ ጉልበተኛነት

**"ያለን ማህበራዊ እውቀት ብቃት ያላቸው አመራሮች ወንዶች ብቻ እንደሆኑ እንድናምን አድርጎናል። መማር አለብን፤ ሴቶች ለስልጣን ከመወዳደር ፈርተው ወደኋላ ሊሉ አይገባም።"**

Theresa Mmolawa